የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ አስተባባሪ ኮሚቴ፣ በሰሜን ካሊፎርኒያ
**Ethio-Sudan Border Committee in Northern California**
**P. O. Box 1482, San Jose, CA 95113**

# የሰሜን ካሊፎርኒያ ኢትዮጵያውያን የድንበር ጉዳይ ውሳኔዎች

**ጁላይ 26፣ 2008**

**<u>ሳንሆዜ፣ ካሊፎርኒያ</u>**

የወያኔ ኢሕአዴግ ፓርቲ ከሰቲት ሁመራ እስከ ጋምቤላ ያለውን የኢትዮጵያ ምዕራባዊ ደንበር ቆርሶ ለሱዳን በመስጠት በሀገራችን ላይ የሚፈፅመውን ደባ በሚመልከት፣ ጁላይ 26፣ 2008 ከ3፡00-7፡00ፒም ድረስ በሳንሆዜ ከተማ ማሶኒክ ሴንተር፣ ሁለት የታሪካና የህግ ባለሞያዎች በተገኙበትና ከተለያዩ የሰሜን ካሊፎርኒያ ከተሞች የመጡ በርካታ ኢትዮጵያውያንን ባካተተ ሕዝባዊ ስብሰባ ሰፊ ወይይት ተካሂዷል።

ስብሰባውን ያዘጋጀው፣ በሰሜን ካሊፎርኒያ የኢትዮ-ሱዳን ድንበር ጉዳይ አስተባባሪ ኮሚቴ ሲሆን፣ የታሪክ መምህር የሆኑት ዶክተር ዳንኤል ክንዴ እና የታወቁት የህግ ባለሞያ፣ ፕሮፌሰር አለም አንተ ገብረሥላሴ በስብሰባው ተገኝተው በጥናት የተደገፈ ሰፊ ማብራሪያና ገለፃ አድርገዋል። ሁለቱ ሊቃውንት በጥናታቸው እንዳቀረቡት፣ በታሪክ የኢትዮጵያ የሆነውን ለም መሬት ቆርሶ ለሱዳን የሰጠው ወያኔም ሆነ ተቀባዩ የሱዳን መንግስት የሚፈፅሙት የስውር ስምምነት ህጋዊነትና ተቀባይነት የሌለው መሆኑን አስረድተዋል። በተጨማሪም፣ በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የሚመራበት ህገመንግስት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የማያስከብር በመሆኑ፣ ድንበራችን ማስከበር የሚቻለው ስንተባበርና በፓለቲካ፣ በዲፕሎማሲና በህግ ሥራዎች ጠንካራ ኃይል ስንፈጥር መሆኑን አስምረውበታል። ከእንግዶቹ በተጨማሪ የአካባቢውን ታሪክ የሚያውቁና በተለያዩ የህላፊነት ቦታዎች የሰሩ ተቆርቋሪዎች የሀገር ፍቅር በተሞላበት ስሜት፣ ለውድ ሀገራችን ደህንትና ለድንበራችን መከበር አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል። በመጨረሻም፤ ከተለያዩ የሰሜን ካሊፎርኒያ ከተሞች፣ ሳንሆዜ፣ ኦክላንድ፣ ሳንፍራንሲስኮ፣ ሳክራሜንቶ፣ ፍሬዝኖና ስታክቶን የመጡ ወገኖቻችን መደማመጥና መከባበር በተሞላበት መንፈስ ውይይቶችን በማካሄድ የሚከተሉትን ውሳኔዎች በአንድ ድምጽ አስተላልፈዋል።

1ኛ. የወያኔ ኢሕአዴግ ፓርቲ ከሰቲት ሁመራ እስክ ጋምቤላ ያለውን የኢትዮጵያን ምዕራባዊ ደንበር ቆርሶ ለሱዳን በመስጠት የሚያካሂደውን ደባ በጥብቅ እናወግዛለን።

2ኛ. የሀገሩን ደንበር ለማስከበር ወገናችን የሚያካሂደውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ ከልብ እንደግፋለን፣ በወያኔና በሱዳን ወታደሮች ለሚፈናቀሉ ወገኖቻችን በሚያስፈልገው ሁሉ ለመርዳት ቃል እንገባለን።

3ኛ. የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች ለወያኔ አገዛዝ መሳሪያ በመሆን ህዝባቸውን እንዳይጎዱ እያሳሰብን፣ ደንበሩን ለማስከበር ከሚታገለው ወገናቸው ጎን እንዲሰለፉ ወገናዊ ጥሪ እናስተላልፋለን።

4ኛ. የወያኔ ኢህአደግ ፓርቲ፣ የሀይማኖት መሪዎችን እያሳደደ፣ የፖለቲካ መሪዎችን እያገደ፣ የብዙሀን መገናኛዎችን እየዘጋ፣ በሀገሪቱ በመሰረተው የአንድ ሰው፣ አንድ ፓርቲ አገዛዝ ከጎረቤት መንግስታት ጋርም ሆነ ከሌሎች ኃይሎች ጋር የሚያካሂደው ድርድርና የሚፈራረመው ውል ኢትዮጵያን የማይወክል በመሆኑ የማንቀበለው መሆናችንን እናስታውቃለን።

5ኛ. የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች በመካከላቸው የሚያካሂዱትን የእርስ በእርስ ግጭት አቁመው የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበር የሚያካሂደው ትግል እንዲተባበሩ ጥሪ እናደርጋለን።

6ኛ. አለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ተቋሞች፣ የሚዲያ አውታሮችና ሌሎችም የብዙሀን ማህበራት፣ የወያኔ አህአዴግ ፓርቲ ህዝባችንን ከመኖሪያ ቦታው፣ ከእርሻውና ከርስቱ በማፈናቀል የሚፈፅመውን ግፍ በማጋለጥ የህዝቡን ድምጽ እንዲያስተጋቡ ጥሪ እናደርጋለን።

7ኛ. የጎረቤት ሀገሮችም ሆኑ ሌሎች መንግስታት፣ የወያኔ ኢሕአዴግን ጸረ ኢትዮጵያ ፖሊሲ በመጠቀም፣ የኢትዮጵያን ድንበር በማፍረስ፣ ንብረቷን በመዝረፍ እንዳይሰማሩ እናስጠነቅቃለን።

8ኛ. የኢትዮ-ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የሚያካሂዳቸውን እንቅስቃሴዎች እንደግፋለን፣ እንተባበራለን፣ በሌሎች ከተሞች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም እንዲተባበሩ ጥሪ እናደርጋለን።

9ኛ. የኢትዮጵያን ድንበር የማስከበር ጉዳይ የመላው ኢትዮጵያ ዜጎች ሀላፊነት በመሆኑ፣ ሁላችንም በያለንበት ደንበሩን ለማሰከበር በመታገል ላይ ያለውን ወገናችን በአንድነት እንድንረዳ ጥሪ እናደርጋለን።

10ኛ. የወያኔ ኢህአዴግ ፓርቲ፣ በአፋር፣ ሀረርጌ፣ ጋምቤላ፣ ባድሜ፣ ወልቃት፣ አርማጭሆ፣ ጭልጋና በሌሎችም አካባቢዎች የሚያካሂደውን ህዝብ የማፈናቀል፣ የማሰርና የማስፈራራት ዘመቻ በጥብቅ እናወጋዛለን።